# ሙሉ ኃይላችንን የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19)ን ጫና ለመቋቋም እናውለው!

የኮሮና ቫይረስ ወረረሽኝን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

የዓለም የጤና ድርጅት (WHO) የኮሮና ቫይረስን (Coronavirus Disease 2019 “COVID-19”) በመጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ.ም ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ መሆኑን አውጇል፡፡ እስከ መጋቢት 14 ቀን 2012 ድረስ በሽታው 195 አገሮችን ያዳረሰ ሲሆን፤ ከ378 ሺህ በላይ ሰዎች በቫይረሱ ተጠቅተዋል፤ ከ16500 በላይ ደግሞ ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ ምንም እንኳን በሽታው መድሃኒትም ሆነ ክትባት ገና ያተገኘለት ቢሆንም በሕክምና እርዳታና ክትትል ከበሽታው አገግመው ወደ ቤታቸው የተመለሱ ሰዎች ቁጥር ከ102 ሺህ በላይ ነው፡፡ ይህም ሰዎች ተገቢ የሕክምና ዕርዳታ እስካገኙ ድረስና በቂ የቅድመ ጥንቃቄ ዕርምጃዎችን ከወሰዱ የበሽታውን ስርጭት መግታት እንደሚቻል አመላካች ነው፡፡ በሽታው በአገራችን መከሰቱን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ጤና ተቋም መጋቢት 4 ቀን 2012 ዓ.ም ባወጡት የጋራ መግለጫ ያሳወቁ ሲሆን እስካሁን አስራ አንድ ሰዎች (ሶስት ጃፓናውያን፣ አንድ እንግሊዛዊ፣ አንድ አውስትራሊያዊ እና 4 ኢትዮጵያውያን) በበሽታው መያዛቸው ታውቋል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ የቫይረሱ ወረርሺኝ በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና የኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ የተለያዩ አደጋዎችን ደቅኗል፡፡

**በማኅበራዊ ዘርፍ**

ኢትዮጵያዊያን በተለምዶ ሰላምታ የምንለዋወጥበት መንገድ፣ ቤተ እምነቶች እና የተለያዩ አገልግሎት የምናገኝባቸው አካባቢዎች ሕዝብ በብዛት የሚገኝባቸው በመሆኑ እና በእነዚህ አካባቢዎች እርስ በርስ በጣም ተቀራርበን ብዙ ንክኪዎች የምንናደርግ መሆናችን ለቫይረሱ ተጋላጭነታችንን ከፍ የሚያደርግ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ ወረርሽኙን በቁጥጥር ስር ማዋል እስኪቻል ድረስ አኗኗራችን ላይ ጠበቅ ያለ ሕይወት አድን ለውጥ ማድረግ አስገዳጅ ሆኗል፡፡

**በፖለቲካ ዘርፍ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ነሐሴ 23 ቀን 2012 ዓ.ም እንዲካሄድ ቀን እንደተቆረጠለት ይታወቃል፡፡ በኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ ስጋት ምክንያት ወረርሽኙ በሀገራችን እንዳይዛመት

መንግሥት ለአጭር ጊዜ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች በምርጫ ጊዜ ሰሌዳው ላይ ከአሁኑ ተጽዕኖ እያሳደሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከየትኛውም የፖለቲካ እቅስቃሴ በፊት የዜጎች ደህንነት ቅድሚያ ማግኘት የሚገባው ጉዳይ በመሆኑ፣ ወረርሽኙን ለመቆጣጠር የተወሰኑትን ውሳኔዎች ሙሉ በሙሉ በመቀበል ከሰኞ መጋቢት 7 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የታቀዱ ማንኛውም ሕዝባዊ ስብሰባዎችንም ሆነ እጅግ አስፈላጊ ያልሆኑ የፓርቲያችን ስብሰባዎችን በሙሉ ላልተወሰነ ጊዜ አቁመናል፡፡ ይህንንም በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ላሉ መዋቅሮቻችን አሳውቀናል፡፡ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ስብሰባዎች በሚደረጉበት ጊዜ የተሳታፊዎች ቁጥር የተመጠነ እንዲሆን፣ ስብሰባውን የሚሳተፉ ሰዎች መደረግ ያለበትን አስፈላጊ ጥንቃቄ የሚያውቁ መሆናቸው እና ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት ጥንቃቄዎቹን መፈጸማቸው እንዲረጋገጥ እና ስብሰባዎቹ በቂ የአየር ዝውውር ባለባቸው ቦታዎች እንዲካሄዱ ለሁሉም መዋቅሮቻችን መመሪያ ተላልፏል፡፡ የጤና ፖሊሲ ቡድናችንም አስፈላጊውን ምክር ለመለገስ በሁሉም ጊዜያት ዝግጁ እንዲሆን መመሪያ ተሰጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ወረርሽኙ እዳይስፋፋ መንግሥት የወሰናቸው ውሳኔዎች እና ወደፊትም የሚወሰኑ ውሳኔዎች የምርጫው የጊዜ ሰሌዳ ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በግልጽ እያሳወቀ እንዲቀጥል እና ምርጫ በሚካሄድበት ቀንም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ማንኛውም ማሻሻያዎች ሁሉንም ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ውይይት እያደረገ እንዲወስን እንጠይቃለን፡፡

ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ ላይ ቆመን አባላት እና ደጋፊዎቻችንን በማስተባበር ወረርሽኙን ለመቆጣጠር አስፈላጊውን ትብብር እንድናደርግ እንጠይቃለን፡፡

በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች በተለይም በቄለም ወለጋ፣ በምዕራብ ወለጋ እና ሆሮ ጉድሩ ዞኖች ጸጥታን ከማስከበር አንጻር የስልክ እና የበይነ መረብ (Internet) ግንኙነት ከተቋረጠ ወራት መቆጠሩ ይታወቃል፡፡ በዚህ ወሳኝ ወቅት የስልክ እና

በይነ መረብ ግንኙነት መኖሩ ዜጎች እራሳቸውን ለመከላከል ስለቫይረሱ ስርጭት ትክክለኛ እና ጊዜውን የጠበቀ መረጃ እንዲደርሳቸው በጣም አስፈላጊ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የስልክ እና በይነ መረብ ግንኙነት አለመኖር በአካባቢው ያለውን የስርጭት ሁኔታ ለመከታተል እና አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ለመንግሥት ሊደርሱት የሚገቡ መረጃዎችን ለመሰብሰብም አዳጋች ያደርገዋል፡፡ ይህን ከግምት በማስገባት መንግሥት በአካባቢው የተቋረጠውን የስልክ እና የበይነ መረብ ግንኙነት ወደሥራ እዲመለስ እንዲያደርግ እያሳሰብን ከዚህ ጋር ተያይዞ ለሚመጣ የጸጥታ እና ደኅንነት ስጋት አማራጭ መፍትሄዎችን በፍጥነት እንዲያዘጋጅ እንጠይቃለን፡፡ እስካሁን ተቋርጦ በነበረው ግንኙነት ምክንያት የተፈጠረውን የመረጃ ክፍተት ለማካካስም በአካባቢው ከሚሰራጩ የመገናኛ ብዙሃን ጋር በመሆን ሰፊ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እንዲሠራ እንጠይቃለን፡፡

መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተውን ወረርሽኝ በቁጥጥር ስር ለማዋል በሚደረገው ጥረት ውስጥ ዓለም አቀፍ ተቋማት እና ለጋሾች ፈጣን ምላሽ እንዲሰጡ በሚደረገው ማግባባት ውስጥ እስካሁን ላደረገው ጥረት እያመሰገንን ግንባር ቀደም ሚና መጫወቱን እንዲቀጥልም አደራ እንላለን፡፡

**በኢኮኖሚ ዘርፍ**

ቫይረሱ መከሰቱ ለዓለም ይፋ ከሆነበት የአውሮፓውያን ያለፈው ዓመት መባቻ ጀምሮ ስርጭቱ በተለያዩ አገራትና በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ላይ ያሳደረው ጫናና ቀውስ ከእለት ወደ እለት እየተባባሰ መጥቷል፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ከውጭ በሚገቡ እንደ ነዳጅ እና የምግብ ሸቀጦች ላይ ጥገኛ ለሆኑ ኢኮኖሚዎች የኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ እያስከተለ ያለው ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ የስፋቱ መጠን እያየለ ነው፡፡ ይህም የኮሮና ቫይረስ ከኅብረተሰብ ጤና ችግርነቱ በላይ ውስብስብ የኢኮኖሚ መቃወስ የሚያስከትል መሆኑን የሚሳይ ነው፡፡

የቫይረሱ ስርጭት በመላው ዓለም የንግድና ምጣኔ ኃብት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ይገኛል፡፡ በአገራችን ኢኮኖሚም ላይ ብርቱ ክንዱን ማሳረፉን ጀምሯል፡፡ ለምሳሌ የአየር በረራዎች መቀዛቀዝ፣ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶች መሰረዝ፣ የቱሪስት ፍሰት መቀነስ በተለይ በአየር መንገዳችን ላይ፣ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ

በተሰማሩት እና እንደ አበባ እና አትክልትና ፍራፍሬ ያሉ በቶሎ ሊበላሹ የሚችሉ ምርቶችን ወደውጭ ላኪ ዘርፍ ላይ ከፍተኛ የሥራ መቀዛቀዝ አስከትሏል። የሰውም ሆነ የሸቀጦች እንቅስቀቃሴ በከፍተኛ ደረጃ መስተጓጎል አጠቃላይ የንግድ መቃወስና የገንዘብ ዝውውር ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳደረ ሲሆን ይህም መጪውን ጊዜ ፈታኝና ለትንበያ አስቸጋሪ እያደረገው ይገኛል። በኮሮና ምክንያት በቅድሚያ የተጎዳው የአገልግሎት ዘርፉ ቢሆንም በሂደት ወደ ግብርናና የኢንዱስትሪ ዘርፍ እንቅስቃሴ መሸጋገሩና በምርት ዕጥረት ምክንያት የኑሮ ውድነት ማሻቀብና ተያያዥ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ መከተሉ አይቀሬ ነው። ይህ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ በጥንቃቄ ካልተያዘ ከ12ዓመት በፊት ከተከሰተው የዓለም የገንዘብ ቀውስ (financial crisis) በላይ ጉዳት ማስከተሉ እንደማይቀር የምጣኔ ኃብት ባለሙያዎች እያሳሰቡ ይገኛል።

የንግድ ድርጅቶች በሚያጋጥማቸው የገቢ መቀነስና ተያያዥ የገቢ ችግሮች ምክንያት የሠራተኛ ቅነሳ ወይም ተመሳሳይ ዕርምጃ ለመውስድ ሊገደዱ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱ ችግር በአገር ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቋቋም አገሮች የተለያዩ ድጋፎችን በተለይም ለግሉ ዘርፍ አንቀሳቃሾች ያደርጋሉ። አሁንም የኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ ተከትሎ የተለያዩ ሀገራት ለሀገራቸው የግል ዘርፍ የቀጥታ የገንዘብ ድጎማ ማድረግን፣ የግብር እፎይታ እና ግብሩ የሚከፈልበትን ጊዜ ማዘግየትንና የግብሩን መጠን መቀነስ የመሳሰሉ ዕርምጃዎችን እየወሰዱ ይገኛል።

አገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት ሦስት ዓመታት በሰላምና ፀጥታ መደፍረስ ምክንያቶች ለኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች መቀዛቀዝ ተዳርጋ ቆይታለች። አገራችን ከገባችበት ቅርቃር ለመውጣት ጥረት በማድረግ ላይ እንደሆነች አንዳንድ ምልክቶች እየታዩ ነበር።

የኮሮና ቫይረስ በሽታ በአገራችን የተከሰተው የብድር እዳ ጫና በአገሪቱ ከመቼው ጊዜ በላይ ባሻቀበበት፤ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ውዝግብ ጫፍ በደረሰበት፣ ሰብል ጨራሽ የአንበጣ ወረርሺኝ በአገሪቱ የግብርና ምርት ላይ ደመና በጋረጠበትና በመንግስት ድጎማ የሚኖረውን የኅብረተሰብ ክፍል ከፍ እንዲል ባስገደደበት ጊዜ ነው። በነዚህ ላይ ከፊታችን ያለው አገራዊ ምርጫ ሲጨመር የአገሪቱን ወጪ ከፍ ያደርገዋል (ለምርጫው ከለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች የተገኘ ዕርዳታ እንዳለ ሆኖ)።

በመሆኑም መንግሥት በሌሎች አገራት የታየውን ያህል ለግሉ ዘርፍ የንግድ ማኅበረሰብ ድጋፍና ለዋና ዋና ልማት አውታሮች የሚውል ቀጥተኛ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ አቅም እንደሚያንሰው ይገመታል፡፡

የግልና የንግድ ዘርፉ ባለፉት ዓመታት የታየው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መቀዛቀዝን ተቋቁሞ የግብር ግዴታውን በሚገባ በመወጣቱ በ2011 የበጀት ዓመት እንዲሁም በ2012 ዓ.ም የመጀመሪያ 6 ወራት ከፍተኛ ግብር እንደተሰበሰበ የገቢዎች ሚኒስቴር በተለያዩ ጊዜያት አስታውቋል፡፡ በሕዝባችን ስጋትና በሸቀጦች እጥረት ላይ የተመሰረተ የትርፍና አቋራጭ መክበሪያ መንገዶችን የሚያሳድዱ ነጋዴዎች እንዳሉ ሁሉ ብዙኃኑ የማኅበረሰቡ ክፍል ግን አግባብ ባለው ሕግ ሥር የሚተዳደርና የሚጠበቅበትን ግብር የሚከፍል እንደሆነ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ለተለያዩ የአገራችን ችግሮች ገንዘብ እንዲለግስ የሚጠየቀው ክፍል ይሄው የኢኮኖሚው ዋና አንቀሳቃሽ ሞተር የሆነው የግል ባለኃብቱ ነው፡፡

በቅርቡም በባንኮች ላይ ተጥሎ የነበረውን አስገዳጅ የ27% የቦንድ ግዢ ፖሊሲ መነሳትን ተከትሎ አንዳንድ ባንኮች ለአገራችን የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ በሚቀርብ ብድር ላይ የነበረውን የወለድ ጣራ ዝቅ እንዲል ያደረጉትን ቅናሽ እንዲሁም ሌሎች አጋዥ ለውጦች የአገራችን የግል ንግድ ዘርፍ እርስ በእርሱ ለመደጋገፍ የሚያደርገው ጥረት ማሳያ ነው፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተደቀኑባትን ፈተናዎች በአሸናፊነት ለመሻገር የሁላችንንም ድጋፍ የምትሻበት ወቅት ላይ ትገኛለች፡፡ ዛሬ የሁላችንም አንድነትና መተባበር መቅደም ያለበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡ ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት ኢዜማ የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን መቆጣጠር እንዲቻል እና በተለይ በኢኮኖሚያችን ላይ የሚያሳድረውን ችግር ለመቀነስ የሚከተለውን ጥሪ ያስተላልፋል፡

- ለአገራችን የግል ዘርፍ፡ የኮቪድ-19 ኢኮኖሚያዊ ጫና ተጽዕኖ የት ድረስና እስከ መቼ እንደሚዘልቅ በአገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ማኅበረሰቡ ዘንድ

በቅጡ ያልታወቀና በሂደት የሚለይ ነው፡፡ ተጽዕኖውን በተቻለ መጠን ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ በእናንተ በኩል የሚጠበቀውን ግልፅ እና ተዓማኒ መረጃ የመስጠት ኃላፊነት በአግባቡ እንደምትወጡ ኢዜማ ያምናል፡፡ ሆኖም እናንተ በአሁኑ ወቅት በመጋፈጥ ላይ የምትገኙትን የኢኮኖሚና የፋይናንስ ቀውስ ሕዝባችን በቤቱ፣ በእለት ተእለት ኑሮው፣ በገቢ ምንጩ፣ በልጆቹና በቤተሰቡ ላይ በርካታ እጥፍ እየኖረው የሚገኝ ሐቅ ነው፡፡ ሕዝባችን በኑሮ ውድነትና ሊከሰት በሚችል የምግብ ምርት አቅርቦት እጥረት ስጋት በተወጠረበት፣ በቤተሰቡ ህልውና ላይ አዲስ ስጋት ባንዣበበት በአሁኑ ወቅት ስጋትን የሚያባብስና ለሕገ-ወጥ መክበሪያ አቋራጭ መንገዶችን ማፈላለግ የዜግነት ግዴታችሁን አለመወጣት ብሎም የሀገር እና ወገን ክህደት መሆኑን እንደምትረዱት እናምናለን፡፡ ከሕዝባችን መካከል በአንዳችን ስጋት ወይም መገለል ላይ የተመሰረተ ያልተገባ ትርፍ የሕዝብ ለሕዝብ ቁርሾና ስር የሰደደ አለመተማመን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለሆነም እንደስካሁኑ አላግባብ ትርፍ አሳዳጆችን ለሕግ በማቅረብና ይህን ፈታኝ ወቅት በጋራ ለመሻገር የሚያስችለንን የኢትዮጵያዊ ዜጋ ተምሳሌትነት እንድታሳዩ ከታላቅ አደራ ጋር እንጠይቃለን፡፡

- **ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት፡** መንግሥት የቫይረሱን ስርጭት ለመቆጣጠር የመደበው 5 ቢሊዮን ብር በጀት ለሚደረገው ርብርብ አውንታዊ አስተዋጽዖ ይኖረዋል፡፡ በቅርቡ በግል ዘርፉ ሊደረጉ የሚችሉ ያልተገቡ የዋጋ ጭማሪዎችን ለመቆጣጠር በመንግሥት የተቋቋመውን ግብረ ኃይል ኢዜማ በመልካም ጎኑ የሚመለከተው ቢሆንም ግብረ ኃይሉ በአሠራሩና በሂደቱ ሁሉንም ባለድርሻዎች የሚያሳትፍ እንዲሆን ጥሪ ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም አገራችን የምትገኝበት ሁኔታ ሁሉንም ማኅበረሰብ የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን የግል ዘርፉን ቁጥጥር እንደሚያስፈልገው አካል ብቻ የሚፈርጅ እይታ ፍትሃዊ እንደማይሆን ግብረ ኃይሉም ሆነ መንግሥት መረዳት እንዳለበት ኢዜማ ያምናል፡፡ ስለሆነም የከቁጥጥር እና ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እርምጃዎች ጎን ለጎን ደጋፊ እርምጃዎችን ማካተት እንዲሁም የኮቪድ-19 በሁሉም የአገራችን ክፍሎች የሚያስከትለውን ትክክለኛ ጫና በመረጃና በጥናት የማወቅ አስፈላጊነት

አጽንዖት ሊደረግበት እንደሚገባ ኢዜማ ሊያሳስብ ይወዳል። የአገራችንን ኢኮኖሚያዊ አቅምና የወቅቱን ፈታኝ ሁኔታ ከሚያገናዝቡ ደጋፊ እርምጃዎች መካከልም የሚከተሉትን መንግሥት እንዲተገብር ኢዜማ ይጠይቃ፤

- ለአገራችን የንግድ ማኅበረሰብ እንደየእርከኑ ሊደረግ የሚችል ጊዜያዊ የግብር እፎይታ መስጠት (የተጨማሪ ዕሴት ታክሶችን የመክፈያ ጊዜ ማራዘም፣ የጡረታ መዋጮዎችን መቀነስ፣ ማቆየትና መተው) የሚለው አማራጭ በዘርፉ ባለሞያዎችና የንግድ ምክር ቤቶች በጋራ ምክክርና መለስተኛ ጥናት ተደርጎበት በፍጥነት ለውሳኔ እንዲቀርብ፣

- በተለይ በከፍተኛ ደረጃ የኮቪድ-19 ኢኮኖሚያዊ ጫና ተጽእኖ ለሚታይባቸው የንግድ ዘርፎች የብድር መክፈያ ጊዜ ማራዘምና የብድር ወለድ ቅናሽን ጨምሮ የብድር ምህረትና ሌሎች ተያያዥ አማራጮች ታሳቢ ተደርገው በተመሳሳይ ለጥናትና ለውሳኔ እንዲቀርቡ ኢዜማ ጥሪ ያደርጋል።

- በከፍተኛ የገንዘብ ዕጥረት እየተሰቃየ የሚገኘውን የንግዱ ማኅበረሰብ ችግር ለመፍታት ብሔራዊ ባንክ ከግል ባንኮች በቦንድ ግዢ የሰበሰበውን ገንዘብ የመመለሻ ጊዜያቸው የተቃረቡትን በፍጥነት ለባንኮቹ ቢመልስ ብዙ የግል ባንኮች የሚያበድሩት ገንዘብ በማጣት ከገጠማቸው ችግር ሊያገግሙ ይችላሉ። በመሆኑም በቦንድ ግዢ ከግል ባንኮች ከሰበሰበው ከ95 ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ የመመለሻ ጊዜው የደረሰውን እና መመለሻቸው የተቃረበውን ቢያንስ በከፊል ለባንኮቹ ቢመልስ ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚቀርበውን ገንዘብ ከፍ ያደርገዋል። ስለዚህ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የተሸከመው ችግር ላይ ኮቪድ-19 በሚፈጥረው ተጨማሪ ተጽዕኖ ምክንያት የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሠራተኞችን ወደመቀነስ፣ የተወሰኑ የሥራ ዘርፎችን ወደማጠፍና ከናካቴው ድርጅቶችን ለመዝጋት ከመገደዱ በፊት

የገጠመውን ከፍተኛ የገንዘብ ዕጥረት ችግር መፍታት ወሳኝ መሆኑን ኢዜማ ከወዲሁ ለማሳሰብ ይወዳል፡፡ ለዚሁም የግል ባንኮች የገዟቸውን እና የመክፈያ ጊዜያቸው የተቃረበውን ቦንዶች መንግሥት በፍጥነት ሊመልስላቸው እንደሚገባ ኢዜማ ያምናል፡፡ የገንዘቡ አለቃቀቅ በሕዝቡ ላይ የኑሮ ውድነት በማያስከትል መልኩ እየተጠና እንዲሆንም በዚሁ እናሳስባለን፡፡

- መንግሥት እስካሁን የቫይረሱ ስርጭትን ለመግታት የወሰናቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊነት በተሻለ ትኩረት እንዲከታተል እንጠይቃለን፡፡ የቫይረሱ ስርጭትን ሊያባብሱ የሚችሉ እንደ ብዙ ሰዎችን በአንድ ቦታ መሰብሰብን (በገዢው ብልጽግና ፓርቲ የሚፈጸመውን ጨምሮ) በአስቸኳይ እንዲያስቆም እናሳስባለን፡፡

- በተጨማሪም በኮሮና ቫይረስ (Covid 19) የሚያዙ ዜጎች ቁጥር ሊጨምር እንደሚችል ታሳቢ በማድረግ በቂ የለይቶ ማቆያ እና በቂ ሕክምና መስጠት የሚያስችል አስፈላጊ ዝግጅት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች እንዲደረግ አበክረን እናሳስባለን፡፡ በከተማችን አዲስ አበባ እና በሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞችም ተገንብተው ለነዋሪዎች ያልተላለፉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በአስቸኳይ የሚገባቸውን ማስተካከያ አድርጎ ለለይቶ ማቆያነት እና ለጊዜያዊ ሕክምና መስጫነት እንዲዘጋጁም እንጠይቃለን፡፡ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው እና በተለያየ ምክንያት ሥራ ላይ ያልሆኑ የሕክምና ባለሞያዎችን መረጃ የማሰባሰብ እና በሚፈለጉበት ጊዜ እና ቦታ በፍጥነት ምላሽ እንዲሰጡ ዝግጁ እንዲሆኑ የማሳወቅ ሥራ ከአሁን በስፋት መሠራት አለበት፡፡

- ለጤና ባለሙያዎች፡ ሙያዊ ግዴታችሁን በመወጣት ላይ ላላችሁ ባለሙያዎች ኢዜማ ያለውን ከልብ የመነጨ ክብር እና ምስጋና ይገልጻል፡፡ ከመድሃኒት አቅርቦትና ስርጭት ጋር ተያይዞ እጥረቶች እና የዋጋ ማሻቀቦችን ለመቆጣጠር እንዲቻል ከሚመለከተው አካል ቁጥጥርና ክትትል

ጋር በመቀናጀት ማኅበረሰቡ የጤና አገልግሎቶችን፤ ለጥንቃቄ የሚረዱ ሙያዊ ምክሮችን ብሎም ተያያዥ አቅርቦቶችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲያገኝ ሙያዊ ግዴታችሁን በታማኝነት መወጣታችሁን እንድትቀጥሉ ኢዜማ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

- ለመገናኛ ብዙሃን፡ በዚህ ወቅት ዜጎች ትክክለኛውን እና ወቅቱን የጠበቀ መረጃ በሚረዱት ቋንቋ ማግኘታቸው ከፍርሃትም ሆነ ከመዘናጋት እንዲቆጠቡ እና አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርገው የቫይረሱን ስርጭት እንዲገቱ ለማስቻል እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ትክክለኛ መረጃ በየወቅቱ በማድረስ እና ዜጎችን በማስተማር መገናኛ ብዙሃን የምትጫወቱት ሚና መተኪያ የሌለው ነው፡፡ ስለዚህም ሁሉም የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ሚና በከፍተኛ ኃላፊነት እና ትጋት እንድትወጡ አደራ እንላለን፡፡

- ለሀገራችን ወጣቶች፡ የቫይረሱን ስርጭት ለመቆጣጠር እና ኅብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲያገኝ በየአካባቢያችሁ እና ማኅበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም የምታደርጉትን እንቅስቃሴ አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ አደራ እንላለን፡፡ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ያሉ የኢዜማ አመራሮች እና አባላት የቫይረሱን ስርጭት ለመቆጣጠር እና ግንዛቤ ለማስጨበጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ንቁ ተሳታፊዎች እንደሚሆኑ በዚህ አጋጣሚ ለማረጋገጥ እንወዳለን፡፡

- በውጭ ሀገር ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን፡ ከውጪ ንግድ መቀዛቀዝ ጋር ተያይዞ የአገራችን የውጭ ምንዛሬ በከፍተኛ መጠን ያሽቆለቁላል፡፡ በአንጻሩ ከቫይረሱ ወረርሺኝ ጋር የተለያዩ የሕክምና ቁሳቁሶች (የኮቪድ-19 መመርመሪያ ኪትን ጨምሮ) እና ሌሎች መሠረታዊ ቁሳቁሶች ፍላጎት ይጨምራል፡፡ በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ወደሀገር ቤት ለወዳጅ ዘመድ የምትልኩትን ገንዘብ በባንክ በኩል ብቻ እድታደርጉ በአጽኖት እንጠይቃለን፡፡

- *ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን:* ሕዝባችን በታሪኩ በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና በሉዓላዊነቱ ላይ የተጋረጡ ፈተናዎችን ተጋፍጦ በድል ተወጥቷል። በተመሳሳይ የአሁኑን አስቸጋሪ ፈተና በአንድነት በመቆም ለመሻገር የጋራ ተግባራችን ወሳኝ ነው። ስለሆነም ሕዝባችን በተለያዩ የተዛቡ መረጃዎች ያልተረጋገጡ/አሳሳች ዜናዎች ሳይረበሽ፣ በአነስተኛ ገቢ በሚተዳደረው የማኅበረሰባችን ክፍል ላይ አላስፈላጊ ጫና በሚፈጥር የሸመታ ባህሪያት እንዳይሳተፍ ጥሪ እናቀርባለን። እንዲሁም ለኮቪድ-19 ከፈተኛ ተጋላጭ በሆኑት የአገራችን አረጋውያን፣ ሕሙማን፣ አካል ጉዳተኞች፣ የጎዳና ተዳዳሪዎችና ለዜናና መረጃ አቅርቦት ሩቅ ለሆኑ ዜጎች የሚገባውን ክብር በሚሰጥ መልኩ የምናደርገውን የዘወትር ድጋፍና እንክብካቤ አጠናክረን እንድንቀጥል ጥሪ እናቀርባለን። የተደቀነብን አስቸጋሪ ወቅት ሁላችንም ውስጥ ያለውን ሰብዓዊነታችንን አጉልተን አውጥተን በአንድ ላይ የምንቆምበት እና የአብሮነታችንን ጥንካሬ የምናሳይበት እንጂ በራስ ወዳድነት እና ስግብግብነት በመነሳሳት እራስን ለማዳን ሸቀጥ በብዛት እየገዙ በማከማቸት አነስተኛ አቅም ያላቸው ዜጎች ላይ ከወረርሽኙ ያልተናነሰ ጫና የምናሳድርበት በፍጹም ሊሆን አይገባም። ቫይረሱ ያለምንም ልዩነት ሁሉንም የሰው ልጅ የሚያጠቃ መሆኑን ከግምት በማስገባት እርስ በርስ የምናደርገውን መደጋገፍ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ በሀገራችን ለሚገኙ የውጭ ሀገር ዜጎችም እንድናካፍል እና እንግዳ ተቀባይነታችንን እንድናስመሰክር እንጠይቃለን።

በመጨረሻም ሁላችንም

- እጃችንን በተደጋጋሚ በውሃና እና በሳሙና መታጠብ፤ ይህ በማይሆንበት ጊዜ እጅን የአልኮል መጠናቸው ከ60% በላይ በሆኑ ንጽሕና መጠበቂያዎች (Sanitizers) በደንብ በማሸት፤
- ማኅበራዊ ፈቀቅታን (Social Distancing) ተግባራዊ ማድረግ (ብዙ ሰው በተሰበሰበበት ቦታ አለመገኘት፣ መጨባበጥን ጨምሮ ከሌሎች ሰዎች ጋር አካላዊ ንክኪ ባለማድረግ)፤
- የህመሙ ምልክት ማለትም:- ትኩሳት፣ ደረቅ ሳል እና ለመተንፈስ መቸገር ካስተዋሉ እራስዎትን ወይንም እንደዚህ ዓይነት ምልክት የታየባቸው ሰዎችን ከሌሎች ሰዎች ንክኪ ማራቅ እና ለብቻቸው

ማቆየት እና 8335 ወይንም 952 ላይ በመደወል ማድረግ የሚገባዎትን መረጃ በመቀበል እና በመተግበር፤

- የኢፌዴሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ጤና ተቋም የሚያወጧቸውን መረጃዎች እና መመሪያዎች በመከታተል እና በመተግበር

እራሳችንን ከቫይረሱ ለመጠበቅ መውሰድ የሚጠበቅብንን ጥንቃቄዎች እንድናደርግ አጥብቀን እየጠየቅን የተደቀነብንን ጊዜያዊ አደጋ አልፈን ዘላቂ ሰላም እና መረጋጋት የሰፈነባት፣ ለሁሉም ዜጎች እኩል ዕድል የምትሰጥ ኢትዮጵያን የመገንባት ጉዟችንን አጠናክረን እደምንቀጥል ልናረጋግጥ እንወዳለን።

ፈጣሪ ሀገራችንን እና ሕዝባችንን ከክፉ ሁሉ ይጠብቅ!

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

መጋቢት 15 ቀን 2012

አዲስ አበባ